የ2006 ዝቅተኛው የሰአት የክፍያ መጠን ሕግ

D.C. Code §§ 2-220.01 – 2-220.11

የኮንትራት ወይም የመንግስት እርዳታ ተቀባዮች በዉሉ መሰረት አገልግሎት ለሚሰጡ ተባባሪ ሰራተኞች እና ንዑስ ተቋራጮች አሁን ካለዉ የሰአት ክፍያ ያላነሰ ክፍያ ይከፍላሉ።

ከጃንዋሪ 1/ 2026 ጀምሮ እስከ ጁን 30/2026 ድረስ ያለዉ የሰአት የክፍያ መጠን በሰዓት $17.95 ነዉ። ከጁላይ 1/2026 ጀምሮ የዲስትሪክቱ ዝቅተኛዉ የሰአት ክፍያ ወደ $18.40 ከፍ ይላል።

ደመወዝን ለመክፈል የተቀመጠው መስፈርት የሚመለከተዉ ነው፡-

- የ **$100,000** መጠን ወይም ከዚያ በላይ የኮንትራትክፍያ የሚቀበሉ ኮንትራክተሮች እንዲሁም ከዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከተቀበሉት ገንዘብ **$15,000** ወይም ከዚያ በላይ የሚቀበሉ ሁሉም ንዑስ ተቋራጮች፣ እና
- የ **$100,000** መጠን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ከዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መንግስት እርዳታ የሚያገኙ እና ተቀባዩ ከሚቀበለዉ የመንግስት እርዳታ **$50,000** ወይም ከዚያ በላይ የሚቀበሉ የነዚህ ተቀባዮች ሁሉም ንዑስ ተቋራጮች፣

“ኮንትራት” ማለት በተቀባዩ እና በዲስትሪክቱ አስተዳደር መካከል የሚደረግ የፅሑፍ ስምምነት ነዉ።

“የመንግስት እርዳታ” ማለት ከኤጀንሲ፣ ከኮሚሽን፣ ከተወካይ ወይም ከሌላ የዲስትሪክቱ አስተዳደር አካል የገንዘብ ጥቅም የሚያስገኝ የእርዳታ፣ ብድር ወይም የታክስ ጭማሪ ፋይናንስ ነዉ።

“ተባባሪ ሰራተኛ” ማለት በቀጥታ ከመንግስት እርዳታ ወይም የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ ሰራተኞችን፣ ማንኛዉም ለመንግስት እርዳታ ወይም ዉል አገልግሎቶችን የሚያከናዉን የተቋራጭ ወይም የንዑስ ተቋራጭ ተቀባይ ሰራተኛን ጨምሮ ከዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ አስተዳዳሪ ጋር በተደረገ ዉል መሰረት ካሳ በሚቀበል የተቀጠረ ግለሰብ ነዉ። “ተባባሪ ሰራተኛ” የሚለዉ ቃል ዉሉን ወይም የመንግስትን እርዳታ በተመለከተ ጊዜያዊ ወይም አስቸኳይ አገልግሎቶች የሚያከናዉኑትን ወይም በተቋራጩ፣ በተቀባዩ ወይም በንዑስ ተቋራጭ የተቀጠሩትን አይጨምርም።

በተወሰነ መልኩ የሰአት ክፍያ ማሻሻያ ህጉ የማይመለከታቸው፡- 1) በዚህ ሕግ ከሚያስፈልገዉ ደመወዝ በላይ የሆኑ በፌደራል ሕግ የሚፈለጉትን የደመወዝ ዉሳኔዎች የሚመለከቱ ዉሎች ወይም ስምምነቶች፣ 2) ነባር እና የወደፊት የየህብረት ስምምነቶች፤ የወደፊት ስምምነቶች ሰራተኞች አሁን ያለውን የኑሮ ሁኔታ ያገናዘበ ደመወዝ ያላነሰ ክፍያ እንዲከፈላቸዉ እስካደረገ ድረስ፣ 3) ቁጥጥር በሚደረግባቸው መገልገያዎች የሚከናወኑ የኤሌክትሪክ፣ የስልክ፣ የዉሃ፣ የፍሳሽ ማስወገጃ ዉሎች፣ 4) በከንቲባዉ የታወጀዉን አስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ወይም ምላሽ ለመስጠት ወዲያዉኑ ለሚያስፈልጉ አገልግሎቶች ዉሎች፣ 5) ሰልጣኙ የሰራተኞችን ቦታ እስካልተካ ድረስ የኬዝ ማናጅመንትና እና ለስራ ዝግጁነት አገልግሎቶችን ጨምሮ ሠርግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን ለሰልጣኞች አገልግሎት ለሚሰጡ ተቀባዮች የተሰጠ ዉል፣ 6) ትምህርት ቤቶች ለእረፍትዝግ በሆኑበት ወቅት የተቀጠሩ ዕድሜያቸዉ ከ22 ዓመት በታች የሆኑ ሰራተኞች ወይም በሳምንት ከ25 ሰዓታት በታች የሚሰሩ የሙሉ ግዜ ተማሪ ሆነዉ የተመዘገቡ፣ 7) በመንግስት እርዳታ የተሰራ ወይም የተሸሻሉ ንብረቶችን የሚይዙ ተከራዮች ወይም የቸርቻሮ ተቋማት፤ ቀጥተኛ የዲስትሪክት መንግስት እርዳታ ደረሰኝ እስካልተገኘ ድረስ፣ 8) ከ50 የማይበልጡ ግለሰቦችን የሚቀጥሩ እና ለ 501(c)(3) ደረጃ ብቁ ያልሆኑ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ሰራተኞች፣ 9) የMedicaid አገልግሎት አቅራቢዎች ለMedicaid አቅራቢዎች ቀጥተኛ የእንክብካቤ አገልግሎት ስምምነቶች፤ የቀጥታ እንክብካቤ አገልግሎቱ በቤት እንክብካቤ ኤጀንሲ፣ በማህበረሰብ
መኖርያ ተቋም ወይም በቡድን ቤት በኩል የአእምሮ እክል ላለባቸዉ ሰዎች Home Care Licensure Act of 1983; D.C. Official Code § 44-501; እና 10) የጤና አገልግሎቶችን ለመስጠት በሚተዳደሩ የእንክብካቤ ድርጅቶች እና በጤና እንክብካቤ ሴፍትኔት አስተዳደር ወይም በMedicaid እርዳታ አስተዳደር መካከል የተደረጉ ዉሎች ወይም ስምምነቶች መሰረት እስካልተሰጡ ድረስ።

የቤት ዉስጥ እንክብካቤ የመጨረሻ ህግ፡- የሰራተኛ ቅጥር አገልግሎት መምርያ ለቤት ዉስጥ እንክብካቤ ሰራተኞች እና የአብሮነት አገልግሎት ለሚሰጡ ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ጥበቃን አራዝሟል። በዚህ ኢንዱስትሪ ዉስጥ ያሉ አሰሪዎች አሁን ለመዝገብ አያያዝ ድንጋጌዎች ተገዢ ናቸዉ። 29 CFR ክፍል 552 ይመልከቱ።

እያንዳንዱ ተቀባይ እና የተቀባይ ንዑስ ተቋራጭ በዚህ ማስታወቂያ ለተሸፈነዉ ለእያንዳንዱ ተባባሪ ሰራተኛ መስጠት እንዲሁም ይህንን ማስታወቂያ በስራ ቦታዉ ላይ ግልፅ በሆነ ቦታ ላይ መለጠፍ አለበት። ሁሉም ተቀባይ እና ንዑስ ተቋራጮች ቢያንስ ለ3 ዓመታት ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ህግ መሰረት በመደበኛ የስራ ሂደት ዉስጥ የተፈጠሩ እና የተያዙ የደመወዝ መዛግብትን ባግባቡ መያዝ አለባቸዉ።

የይግባኝ ጥያቄ ለማቅረብ፡-በዲሲ የስራ የቅጥር አገልግሎቶች መምርያ የሰአት ክፍያ ቢሮ: **400 Virginia Avenue, SW, 4th Floor, Washington, D.C. 20024** ይጎብኙ፣ በ **(202) 671-1880** ይደዉሉ ወይም የይግባኝ ጥያቄዎን በኦንላይን **does.dc.gov** ያቅርቡ ወይም። **“File a Claim”** ታብ ይግብኙ።